# የተልዕኮ ፖለቲካ አይበጀንም!

**አሜን ተፈሪ** 09-05-17

ማህበራዊ ሚዲያ እንደ ሌሎች ነባር የብዙሃን መገናኛዎች አይደለም። ይህ ሚዲያ ሁሉንም አካባቢዎች በአንድ ጊዜ መሸፈን የሚያስችል አቅም እንዳለው አይተናል። የማህበራዊ ሚዲያ ከነባር እና ከ<<ኦን ላይን>> ሚዲያዎች በእጅጉ የተለየ ነው። ይህ ሚዲያ እንደ ሌሎች ነባር የብዙሃን መገናኛዎች ሙያዊ እና ሥነ ምግባራዊ ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ባህርይ የለውም። ይህ ሚዲያ ስሜትን ተቀጣጣይ ቁሳቁስ የማድረግ አሰራር ያለው ነው -([Weaponizing] emotion)።

በተጨማሪም፤ የመረጃ ቴክኖሎጂ በህዝብ እና በመንግስት መካከል ያለውን ግንኙነት በእጅጉ ቀይሮታል። የመረጃ ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ምህዳርን እንዲለወጥ አድርጎታል። በመሆኑም የተለየ መዋቅር ያለውን ይህን ሚዲያ በወጉ ለመርመር እና ለማስተዳደር ወይም ለመረዳት የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር ያስፈልገናል። በዚህ ረገድ የቴክኖሎጂው ባለቤት የሆኑ ሐገራት እና ምዕራባዊ መንግስታትም በእጅጉ ተቸግረው እናያቸዋለን።

ማህበራዊ ሚዲያ በመንግስት አስተዳደር ጎልቶ የሚታይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳለው ሁሉ፤ ኢ-አስተዳደርን (e-governance) በማስፈን፤ ህዝቡ አርኪ አገልግሎት ለማግኘት የሚችልበት ሁኔታን አመቻችቷል። መንግስት ይበልጥ ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ወይም ህዝቡ መረጃን በቀላሉ ለማግኘት የሚችልበትን ዕድል አመቻችቷል። ማህበራዊ ሚዲያ በዚህ ረገድ ትልቅ ሚና ያለው ነው።

የመንግስት መረጃዎችን ህዝቡ በቀላሉ እና በፈጣን አኳኋን ማግኘት የሚችልበት ሚዲያ በመሆኑ፤ ህዝቡ በመንግስት አስተዳደር ሂደት ንቁ ተሳታፊ ለመሆን ያስችለዋል። የህዝብ ተሳትፎን በማነቃቃት እና የመንግስት አሰራር ግልጽነትን እንዲላበስ በማድረግ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት መጎልበት ትልቅ ሚና ይጫወታል። በተቃራኒው <<ለክሮስፖንዳስ ፖለቲክስ>> መድረክ ፈጥሯል። ከቦታ እና ከጊዜ ተጽዕኖዎች ነጻ የወጣ የኮሙዩኒኬሽን ስርዓት በመሆኑ፤ ከቦታ እና ከሁኔታ የተነጠሉ የፖለቲካ ቡድኖች፤ ስሜትን እንደ ተቀጣጣይ ቁሳቁስ በመጠቀም በህዝብ ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ የሚችሉበትን ሁኔታ ፈጥሯል። የ2008 የብሔራዊ ፈተና ጉዳይን ማስታወስ ይቻላል። ጋጠወጦች በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ባለተስፋ ወጣቶች ህይወት እና በሐገር ሐብት መቀለድ የሚችሉበትን ሁኔታ አይተናል። ይህን ማድረጋቸውንም እንደ ታላቅ ጀብድ ቆጥረውት <<ይህን ያደረግኩት እኔ ነኝ>> ብለው ሲሸልሉ እና ሲፎክሩ አይተናል።

አምና ሆነ ዘንድሮ እንደተመለከትነው የረባ ህልም የሌላቸው ሰዎች የአድማ ጥሪ እያስተላለፉ የህዝብን ጥቅም የሚጎዳ፣ የህግ የበላይነትን የሚጻረር፣ የዴሞክራሲ ስርዓትን የሚፈታተን፣ ሰላምን የሚያውክ አፍራሽ ተግባር ለማከናወን የሚችሉበትን ምቹ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል። በቅርቡ እንደተመለከትነው የአድማ ጥሪ ማስተላለፊያ መድረክ ሆኖ፤ የረባ ህልም የሌላቸው ሀኬተኞች በህዝብ ምርጫ ስልጣን የተረከበን መንግስት አግተው ለመያዝ ሲሞክሩ አይተናል። ማህበራዊ ሚዲያዎች የስሜት ጦር መሣሪያ ማምረቻ ሲሆኑ አይተናል። ለአምስት ቀናት የሚቆይ የአድማ ጥሪ ሲተላለፍ እና በተወሰኑ አካባቢዎች ሲተገበርም አስተውለናል።

ይህ እንዳለ ሆኖ አንድ እውነት በግልጽ መቀመጥ አለበት። የጸረ ሰላም ኃይሎች የሚያስተላለፉት የአድማ ጥሪ ሰሚ የሚያገኘው፤ ህዝቡ በተጨባጭ ያሉበትን ቅሬታዎች የሚፈታለት አጥቶ መተንፈሻ አጋጣሚ ሲፈልግ ነው። የአድማ ጥሪ አስተላላፊዎች የህዝቡን ተስፋ የሚገዛ የፖለቲካ ፕሮግራም ወይም ሐገርን የሚነቃ ራዕይ የያዙ ባለመሆናቸው፤ እንደ ተውሳክ በህዝብ ቅሬታ ላይ ጥገኛ ሆነው የሚኖሩ ናቸው። በመሆኑም ዋና ትኩረታችን የእነዚህን ቡድኖች የአድማ ጥሪ እንዳይሰማ

ማድረግ አይደለም። ዋና ትኩረታችን አስተዋይ የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ በመልካም አስተዳደር፣ በዴሞክራሲያዊ መብቶች አጠቃቀም የሚያነሳቸው ቅሬታዎች እንዲፈቱ ማድረግ ነው።

መንግስት ይህን ጉዳይ በውል ተረድቶታል። ባለፈው ዓመት የተፈጠረውን ሁከት ያስተናገደው <<የዘመድ ቄስ እየፈታ ያለቅሳል>> በሚያሰኝ አግባብ ነበር። የህዝቡን ብሶት፤ ከህዝቡ እኩል በሆነ ምሬት እየተንገበገበ ተገቢነቱን ሲናገር ነበር። በቅርቡ የተስተዋለውን አድማ አስመልክተው አስተያየት የሰጡ የመንግስት ባለሥልጣናትም ክስተቱን ያስተናገዱት በዚሁ አግባብ ነበር። ስለሆነም ለአንዳንድ የብዙሃን መገናኛ በሰጡት አስተያየት ትኩረት ያደረጉት በአድማው ህገ ወጥነት ላይ አይደለም። የተጠራው አድማ ህገ ወጥ መሆኑን አጥተውት አይደለም። ከመነሻው፤ አድማው የተጠራው በሐገር ውስጥ በሚገኝ፣ በህጋዊ መንገድ ተመዝግቦ በሚንቀሳቀስ እና በሰላማዊ ትግል በሚያምን የፖለቲካ ቡድን አይደለም። ተቃውሞን ለመግለጽ የሚያስብ ቡድን ማሟላት የሚገባውን በህግ የተቀመጡ መስፈርቶችን በሟሟላት የተጠራ ተቃውሞ አይደለም።

ባለሥልጣናቱ በሰጡት አስተያየት በዚህ መሰል ጉዳዮች ላይ ትኩረት አላደረጉም። እንደሚታወቀው፤ በሐገሪቱ ህግ <<ለህዝብ የማያቋርጥ አገግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች>> ወይም <<እጅግ አስፈላጊ የህዝብ አገልግሎት ድርጅቶች>> አድማ ማድረግ አይችሉም። ለህዝብ የማያቋርጥ አገልግሎት ከሚሰጡ ድርጅቶች መካከል፤ የህዝብ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ይገኙበታል። እንዲሁም የመንግስት መሥሪያ ቤት ሠራተኞችም የአድማ ሥራ ተሳታፊ ሊሆኑ አይችሉም። ሆኖም <<ከቪኦኤ>> ጋር ቃለምልልስ ያደረጉ እና የመንግስት ሠራተኛ የሆኑ አንድ ሰው፤ <<እኛ በአድማው ተሳታፊ ለመሆን ብንፈልግም አልቻልንም>> በማለት መብታቸው እንደ ተጣሰ ሲናገሩ ሰምተናል። ባለሥልጣናቱ እንዲህ ያሉ ጉዳዮችን በመዘርዘር አልተጠመዱም። በተቃራኒው፤ ትኩረት አድርገው የተናገሩት <<በመንግስት ላይ ቅሬታ ያላቸው ወገኖች ተቃውሞአቸውን መግልጽ ወይም አድማ ማድረግ ይችላሉ። ነገር ግን የአድማው ተሳታፊ ለመሆን የማይፈልጉ ሰዎችን መብት ማክበር ይኖርባቸዋል>> የሚል አስተያየት ነው የሰጡት።

በተመሳሳይ፤ ባለፈው ዓመት በአማራ ክልል የታየውን የተቃውሞ ሰልፍ አስመልክቶ አስተያየት የሰጡ የመንግስት ኃላፊዎችም፤ በሁነቱ ላይ አስተያየት ሲሰጡ፤ ትኩረት ያደረጉት፤ የተቃውሞ ሰልፉ ህጋዊ ፈቃድ ያልተሰጠው እና በሚመለከተው አካል ዕወቅና ያላገኘ ሰልፍ ከመሆኑ ላይ አይደለም። የሐገሪቱን ህዝቦች አንድነት የማያንጸባርቅ እና የኢፌዴሪ መንግስት መገለጫ ያልሆነ ባንዲራ ይዘው በመውጣታቸው ላይ አይደለም። እንዲሁም የጦር መሣሪያ ይዞ በሰላማዊ ሰልፍ መሳተፍ እንደማይቻል በመግለጽ ላይ አላተኮሩም። ይልቅ፤ ሰልፉ ሰላማዊ ሆኖ የተጠናቀቀ>> መሆኑን እና ህዝቡ ተቃውሞን የመገለጽ መብቱ በህገ መንግስቱ የተረጋገጠለት መሆኑን በማብራራት ሲወሰኑ  አይተናል።

በቅርቡም የኦሮምያ የኮሙዩኒኬሽን ኃላፊ <<የፈለገ ሰው አድማ ማድረግ ይችላል። ሆኖም በዚያው መጠን በአድማው ተሳታፊ ለመሆን የማይፈልጉ ሰዎችን መብት ማክበር ይኖርባቸዋል። መንግስት በአድማው ተሳታፊ ለመሆን የማይፈልጉ ሰዎችን መብት የማስከበር ግዴታ አለበት>> ሲሉ ምላሽ መስጠታቸው አይዘነጋም። የመንግስት ኃላፊዎች እንዲህ ያለ አስተያየት የሚሰጡት፤ ገዢው ፓርቲ ራሱ አምኖ የተቀበላቸው ችግሮች በመኖራቸው እና ፓርቲው የሚያውቃቸው ችግሮች እንዲስተካከሉ ህዝቡ በመንግስት ላይ ጫና እንዲያሳድር ፍላጎት ስላለው እንጂ ህገ ወጥ እንቅስቃሴ መሆኑን ባለመረዳት አይደለም።

ኢህአዴግ መቀሌ ባካሄደው የጠቅላላ ጉባዔው ማጠቃለያ ባቀረበው የአቋም መግለጫ፤ ሕዝቡ ከነ ቅሬታው የመረጠው መሆኑን ጠቅሶ፤ በመንግስት ኃላፊዎች ዘንድ የሚታዩ የኪራይ ሰብሳቢነት ችግሮች፣ የመልካም አስተዳደር ጉድለቶች እና ፀረ ዴሞክራሲ አመለካከቶች ይወገዱ ዘንድ ህዝቡ የበኩሉን ግፊት እንዲያደርግ ወይም ጫና እንዲያሳርፍ የትግል ጥሪ ማስተላለፉን እናስታውሳለን። ሆኖም መንግስት የህግ የበላይነትን የሚያራክስ፣ የህዝብ ሰላም እና ጸጥታን የሚያውክ እንቅስቃሴ

እንዲፈጠር ፍላጎት የለውም። መንግስት የህግ የበላይነትን እና የህዝብ ጸጥታን የማስከበር ግዴታ አለበት። ይህን የማስከበር ጉዳይም የምርጫ ጉዳይ አይደለም። ግዴታው ነው። ስለሆነም መንግስት በማናቸውም ምድራዊ ምክንያት የህግ የበላይነትን የሚያራክስ አሰራርን ሊከተል አይችልም።

በዛሬዋ ኢትዮጵያ ሰላማዊ ሰልፍ እና አድማ ማድረግ በህግ የተፈቀደ መብት ነው። ተቃውሞን በይፋ መግለጽ ይቻላል። ተቃውሞን የመግለጽ ጉዳይ መብት እንጂ ችሮታ ሊሆን አይችልም። ስለሆነም አምና ሆነ ዘንድሮ ህዝቡ ተቃውሞውን የመግለጽ መብቱ የተከበረ ነው። ይህ ጉዳይ በግልጽ ከተቀመጠ በኋላ፤ በመብት አተገባበሩ ሂደት የሚታዩ ችግሮችም በግልጽ ሊቀመጡ ይገባል። የተበላሸ አካሄድም በግልጽ መቀመጥ ይኖርበታል።

ይህ ባለመደረጉ አንዳንድ ወገኖች <<መንግስት ዜጎች ተቃውሞአቸውን የመግለጽ መብት አላቸው እያለ ሳለ፤ ሰዎችን እያሰረ ነው>> በማለት መንግስት የሚወስዳቸው እርምጃዎች ህገ ወጥ ስለመሆናቸው ሲናገሩ እንሰማለን። ከሁሉ አስቀድሞ በአንዳንድ አካባቢዎች የተመለከትነው አድማ ህጋዊ አልነበረም። ስለዚህ የሚታሰሩ ሰዎች ቢኖሩ ሊገርመን አይገባም። አንድ ቡድን ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል። አንድ ቡድን ከሚመለከከተው አካል ፈቃድ አግኝቶ፤ ለአፈጻጸሙ ሙሉ ኃላፊነት ወስዶ የሚያካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ ከሆነ፤ ተቃውሞው በሰላማዊ አኳኋን እንዲያከናወን የጸጥታ ኃይሎች ድጋፍ ይሰጠዋል። በሰላማዊ መንገድ የሚገልጸውን አመለካከት ከማይደግፉ ወገኖች ጥቃት ሊደርስብኝ ይችላሉ የሚል ሥጋት ሳይኖረው፤ አቋሙን የማንጸባረቅ ዕድል ያገኛል። በዚህ አግባብ፤ የሰላማዊ ሰልፍ ፈቃድ ያገኙት ቡድኖች መብት ሳይጣስ እና ከማናቸውም የተቃዋሚ ኃይል ጉዳት ሳያገኛቸው ተቃውሞአቸውን መግለጽ የሚችሉበት ሁኔታ ይመቻቻል።

ታዲያ ይህ ሊሆን የሚችለው፤ ሰላማዊ ሰልፉ ህጋዊ አካሄድን በተከተለ ሁኔታ የተጠራ ሲሆን ነው። የተቃውሞ ሰልፉ በሰላማዊ እና ዴሞክራሲያዊ መድረኩ ተሳታፊ ለመሆን በወሰነ ህጋዊ ቡድን የተጠራ ሰልፍ ሲሆን ነው። የዴሞክራሲያዊ መድረኩ የሚያገለግለው በህግ አጥር ውስጥ ተወስኖ ለመንቀሳቀስ ለሚፈልግ ቡድን እንጂ የዴሞክራሲያዊ ስርዓቱን በማናቸውም የአመጻ አካሄድ ለማፍረስ ለሚዘት ኃይል አይደለም። ስለሆነም፤ ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በኃይል የማፍረስ ዓላማ ባለው ቡድን የተጠራ የተቃውሞ ሰልፍ ወይም አድማ ህጋዊ ሊሆን አይችልም። የመንግስት ኃላፊዎችም ይህን በትክክል ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል።

ይሁንና ባለስልጣናቱ ትኩረት ሰጥተው የተናገሩት፤ ዜጎች ተቃውሞአቸውን የመግለጽ መብት ያላቸው መሆኑን እንጂ የአድማ ጥሪው የመጣው ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በኃይል ለማፍረስ በይፋ በሚዝት እና ይህን ለማስፈጸም በይፋ በሚንቀሳቀስ ቡድን (ግለሰብ) መሆኑን አይደለም። ኃላፊዎቹ ህዝቡ ተቃውሞን በይፋ የመግለጽ መብት ያለው መሆኑን እና የአድማው ተሳታፊ ለመሆን የማይሹ ሰዎች መብትም ሊከበር እንደሚገባ ከማሳሰብ አልፈው፤ አድማው ህጋዊ አለመሆኑን በአጽንዖት መግለጽ የሚገባቸው ቢሆንም፤ መንግስት የህዝቡን ችግር ለመረዳት ያለውን ቀና መንፈስ በሚያመለክት አኳኋን ምላሽ ሲሰጡ አይተናል። በዚህ የተነሳ፤ የስርዓቱን መውደቅ የሚናፍቁ ሚዲያዎች አድማውን ህጋዊ በማስመሰል፤ <<መንግስት በአድማው የተሳተፉ አንዳንድ ሰዎችን አሰሯል>> የሚል ሙግት በማንሳት አድማውን ህጋዊ ለማስመሰል ሲሞክሩ ታዝበናል።

ከሁሉ አስቀድሞ አድማው በህገ ወጥ ቡድን የተጠራ ህገ ወጥ አድማ ነው። ይህ አድማ የተጠራው በውጭ ሐገር ሆነው <<የክሮስፖንዳስ ፖለቲክ>> በሚያካሂዱ ሰዎች በመሆኑ ብቻ ተቃውሞው ህጋዊነት የለውም። በዚህ ሂደት ተሳታፊ የሚሆኑ ወገኖችም ህጋዊ ሊሆኑ አይችሉም። ከዚህ በተጨማሪ አድማውን በኃይል እርምጃ ጭምር ተፈጻሚ ለማድረግ የሚንቀሳቀስ፣ በህቡዕ የተደራጀ እና ራሱን <<ቄሮ>> ሲል የሚጠራ ኃይል ተሳትፎ ያደረገበት አድማ መሆኑም ግልጽ ነው። የዚህ ቡድን

አሰራር እና አድራጎት ከሽብር ቡድኖች ጋር የሚዛመድ ባህርይ ያለውም ነው። እንዲህ ያለ አሳሳቢ ገጽታ የሚታይበት እና በህቡዕ በተደራጀ ኃይል የተደገፈ ህገ ወጥ እንቅስቃሴ በመሆኑ መንግስት በቸልታ ሊመለከተው አይችልም። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚታሰሩ ሰዎች ቢኖሩ እርምጃው አነጋጋሪ ሊሆን ወይም ህግ ጥሰት ተደርጎ ሊታይ አይችልም።

ህዝቡም በመንግስት አሰራሮች ላይ የሚኖረውን ቅሬታ ለመግለጽ ሲያስብ፤ በውጭ ሐገር ከተቀመጡ፣ ህጋዊ ካልሆኑ እና በህቡዕ ከተደራጁ ቡድኖች ጋር ባለመተባበር እና ባለመጎዳኘት፤ በብዙ መስዋዕትነት ያገኘውን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንደ ዓይን ብሌኑ ሊጠብቅ ይገባል። ህዝቡ የህግ የበላይነትን በማራከስ ለመሄድ ከሚሞክሩ እና ዓላማቸውን በኃይል ለማስፈጸም ከሚንቀሳቀሱ ቡድኖች ኪሳራ እንጂ ትርፍ እንደማይገኝ አውቆ ሊታገላቸው ይገባል። እነዚህ ቡድኖች ማንነታቸውን በተግባር አሳይተውናል። መብት ይከበር ባዮች ሆነው ፤ የሌሎችን መብት ሲጥሱ አስተውለናል። የጠሩት አድማ ተሳታፊ ለመሆን ባልፈለጉ ሰዎች ላይ ጥቃት ሲያደርሱ ተመልክተናል።

የአድማ ጥሪ ያስተላለፉት እና አመራርም የሚሰጡት ወገኖች በህዝብ ድምጽ የተመረጠ መንግስትን በኃይል እርምጃ የመጣል ዓላማ ያላቸው መሆናቸው በግልጽ የሚታወቅ ነው። ይህ ጉዳይ ብቻ አድማውን እና ተቃውሞውን ህገ ወጥ ያደርገዋል። በህግ ጥላ መንቀሳቀስ የማይሹ እና መንግስትን በኃይል ለመጣል የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች፤ በሰላማዊ - ህጋዊ መድረኩ ሊስተናገዱ የሚችሉ አይደሉም። ሰላማዊ እና ህጋዊ መድረኩ የሚያገለግለው፤ በህጋዊ ጎዳና ለመጓዝ ለወሰኑ ዜጎች ብቻ መሆኑም መዘንጋት የለበትም። ይሁንና ለአመጻ የተሰለፉ ሆነው ሳለ እንደ ሰላማዊ - ህጋዊ አካል በዴሞክራሲያዊ መድረኩ ለመጠቀም ይፈልጋሉ። መንግስትን በኃይል የመጣል ዓላማ ይዘው እንደሚንቀሳቀሱ ሳይደብቁ በይፋ እየተናገሩ፤ <<መንግስት ዴሞክራሲያዊ መብታችንን አላከበረም>> በማለት ያወግዛሉ። እንዲህ ዓይነት አካሄድ የሚከተሉ ከሆነ መንግስት በሰላማዊ መድረክ ሊያስተናግዳቸው አይገደድም። ከእንዲህ ያሉ ቡድኖች ጋር አባሪ ተባባሪ ሆኖ መገኘትም በህገ የሚያስጠይቅ ይሆናል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ህዝቡ በመንግስት ላይ ተጽእኖ መሳረፍ ይችላል። ከዚያም ባሻገር በምርጫ ካርዱ ስልጣን የሰጠውን የፖለቲካ ፓርቲ ከኃላፊነት ማንሳት ይችላል። ሆኖም ይህን የሚያደርገው፤ የህገ ወጥ ቡድኖችን ጥሪ በመቀበል የአድማ እንቅስቃሴ ተሳታፊ በመሆን ሳይሆን በምርጫ ካርዱ ነው። ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱ ጸንቶ ሊዘልቅ የሚችለው በዚህ መንገድ በመጓዝ ነው። ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱን አደጋ ላይ የሚጥል አካሄድ የሚጎዳው በስልጣን ላይ የተቀመጡትን ሰዎች ሳይሆን ህዝቡን ነው። እንደኛ ሺህ ዓመታትን በአፈና ስርዓት ሲዳክር የቆየ ህዝብ እንዲህ ዓይነት ስህተት ሊፈጽም አይገባም። ህዝቡ ይህን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት የፈጠረው በከባድ መስዋዕትነት መሆኑን መዘንጋት የለበትም። እንደ ህዝብ በዚህ ረገድ ከተሳሳትን፤ መልሶ ለማቃናት እጅግ የሚያስቸግር ሁኔታ ውስጥ እንገባለን። ስለዚህ ህዝቡ ራሱን ከዚህ አደጋ ነቅቶ መጠበቅ ይኖርበታል። ጎዳናውን ለህገ ወጥ ቡድኖች ክፍት ማድረግ የለበትም። ይልቅስ በዚህ መንገድ ሊመጡ ለሚሹ ቡድኖች የማይቀመስ ህዝብ መሆኑን ማሳየት ይኖርበታል። እንኳን ምድራዊ ሰው፤ ሰማያዊ መልአክም ቢሆን ከዴሞክራሲያዊ፣ ሰላማዊ እና ህጋዊ አካሄድ ባፈነገጠ ጎዳና ሲመጣ ማውገዝ ይኖርበታል። በስልጣን ጥም እየተገፉ የሚመጡ ተኩላዎችን መከላከል የሚችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው።